መልእክት ሦስት

**የዮርዳኖስን ወንዝ መሻገርና ለውጊያ መዘጋጀት**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ኢያ. 3፡1—4፡24፤ 5፡1-10

I. **ኢያሱ 3፡1—4፡24 የእስራኤል ሕዝብ የዮርዳኖስን ወንዝ የመሻገራቸው ዘገባ ነው፦**

ሀ. የእስራኤል ሕዝብ የአምላካቸውን የቃል ኪዳን ታቦትና ሌዋውያን ካህናቱ ታቦቱን ተሸክመው ሲያዩ፣ ከሥፍራቸው ተነሥተው ተከተሉት—3፡3፣ 6፦

1. ታቦቱ የሦስታንዱ አምላክ አካል መልበስ የሆነው የክርስቶስ ምሳሌ ነበር—ዘጸ. 25፡10-22።
2. የእግዚአብሔር ታቦት ከእስራኤል ልጆች ጋር በሄደ ጊዜ፣ ቅድሚያውን በመውሰድና ወደ ውኃው ውስጥ ለመግባት የመጀመሪያው በመሆን ሦስታንዱ አምላክ አብሯቸው ሄደ—ኢያ. 3፡8፣ 11።
3. ታቦቱ በካህናቱ ትከሻ ላይ መሆኑ፣ በምሳሌ ታቦቱን የተሸከሙት ካህናት ከሦስታንዱ አምላክ ጋር አንድ አካል መሆናቸውን ያመለክታል—ቁ. 3፦

ሀ. እነርሱና እግዚአብሔር አንድ ብዙዎች የተካተቱበት ማንነት—ብዙዎች የተካተቱበት አምላክ-ሰው ነበሩ።

ለ. እግዚአብሔር በእነርሱ መራመድ ተራመደ፣ እነርሱም በእግዚአብሔር መራመድ ተራመዱ።

ለ. የዮርዳኖስ ወንዝ የክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ በምሳሌ ያሳያል—ሐዋ. 2፡23-24፤ 3፡15፦

1. የጌታ የቃል ኪዳን ታቦት ከሕዝቡ በፊት ወደ ዮርዳኖስ ውስጥ ተሻገረ—ኢያ. 3፡11።
2. ታቦቱ ወደ ዮርዳኖስ ውስጥ መግባቱና መውጣቱ የክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ ያመለክታል—ቁ. 15፤ 4፡11።

ሐ. እስራኤል የዮርዳኖስን ወንዝ መሻገሩ የአማኞችን በአካል መሞት ሳይሆን አሮጌው ሰው ያከተመበትን እና የተቀበረበትን የክርስቶስን ሞት አማኞች መለማመዳቸውን በምሳሌ ያሳያል—ሮሜ 6፡3-6፤ ገላ. 2፡20፦

1. በምሳሌ መሠረት፣ የዮርዳኖስ ወንዝ አማኞች ወደ ውስጡ የተጠመቁበትን የክርስቶስን ሞት ያመለክታል—ሮሜ 6፡3-4።
2. የእስራኤል ልጆች አሮጌው ሰዋቸውን ለመቅበርና በክርስቶስ አዲስ ሰው ለመሆን በክርስቶስ ሞት ውስጥ አለፉ—2 ቆሮ. 5፡17፦

ሀ. ወደ መልካሚቱ ምድር ለመግባት፣ ምድሪቱን እንደ ርስታቸው ለመውሰድ እና ከከነዓናውያን ጋር ለመዋጋት ዝግጁ ነበሩ፤ ሆኖም ግን በአሮጌው ሰዋቸው ድሉን ማግኘት አልቻሉም።

ለ. በምሳሌ፣ በክርስቶስ ሞት ተቀብረው ነበር፣ ከዚያም መንፈሳዊውን ውጊያ ለመዋጋት በክርስቶስ አዲስ ሰው ለመሆን በክርስቶስ ትንሣኤ ከሞት-ተነሥተው ነበር—ኤፌ. 6፡10-20።

ሐ. አሮጌው ሰዋችን፣ ተፈጥሮአዊ ሰዋችን፣ ክርስቶስን ለማትረፍ መንፈሳዊውን ውጊያ ለመዋጋት ብቁ እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልገናል፤ በክርስቶስ ውስጥ ከእንግዲህ አዲስ ሰው ነን እንጂ አሮጌው ሰው አይደለንም—4፡22-24።

3. የዮርዳኖስን ወንዝ እንደ መሻገር የአማኞች ወደ ክርስቶስ ሞት ውስጥ መጠመቅ አማኞችን ወደ ክርስቶስ ትንሣኤ ውስጥ ይመራቸዋል—ሮሜ 6፡3-6፤ ቆላ. 2፡12፦

ሀ. በመቀበር ገጽታው፣ ጥምቀት የአሮጌው ሰዋችን መወገድ ነው።

ለ. በትንሣኤ ገጽታው፣ ጥምቀት በመለኮታዊው ሕይወት በክርስቶስ ሕያዋን የተደረግን እንሆን ዘንድ የመንፈሳችን መወለድ ነው—ዮሐ. 3፡6፣ 15፤ ሮሜ 8፡10።

ሐ. በትንሣኤ ክልል ውስጥ ለእግዚአብሔር ኢኮኖሚ መፈጸም በውስጡ የምንመላለስበትን እንዲያውም እየተተከልንበት እና እየተገነባንበት ያለውን ክርስቶስ ሁሉን እንዳካተተው ምድር እንደሰታለን—6፡4፤ ቆላ. 2፡7።

መ. እስራኤል ዮርዳኖስን መሻገሩና ወደ መልካሚቱ ምድር መግባቱ በኤፌሶን መጽሐፍ እንደ ተገለጠው የአማኞችን በክርስቶስ ውስጥ ያሉትን የበረከቶች ብልጥግናዎች ተግባራዊ ልምምድ በምሳሌ ከሚያሳየው ከእስራኤል መልካሚቱን ምድር መውረስና መደሰት ጋር ይገናኛል—ኢያ. 4፡1።

ሠ. ዮርዳኖስን ከመሻገር በኋላ እስራኤል ወደ መልካሚቱ ምድር መግባቱ አማኞች ሰይጣንና የጨለማ ኃይሉ ያሉበትን ሰማያዊውን ስፍራ የመቆጣጠራቸውን ልምምድ ያመለክታል—ኤፌ. 2፡2፤ 6፡12።

II. **አሥራ-ሁለት ድንጋዮች ከዮርዳኖስ ተወሰዱ፣ ሌላም አሥራ-ሁለት ድንጋዮች በዮርዳኖስ ውስጥ ተተከሉ—ኢያ. 4፡3-9፦**

ሀ. ከዮርዳኖስ የተወሰዱት አሥራ-ሁለቱ ድንጋዮች የአዲሱን እስራኤል አሥራ-ሁለት ነገዶች ያመለክታሉ—ቁ. 3-7።

ለ. ድንጋዮቹ ከዮርዳኖስ ውኃ መነሣታቸው ከሞት መነሣትን ያመለክታል—ቁ. 7፦

1. እነዚህ አሥራ-ሁለት ድንጋዮች "ከሞት የተነሣው" አዲስ እስራኤል የሞት ውኃን የመሻገር ምስክር እንደሚሆን በማሳየት ምልክት ነበሩ—ቁ. 6-7፣ 21-24።
2. ይህ አማኞች ከክርስቶስ ጋር ከሞት-መነሣትን መለማመዳቸውን በምሳሌ ያሳያል—ሮሜ 6፡3-4።

ሐ. በዮርዳኖስ መካከል የተተከሉት ሌሎቹ አሥራ-ሁለት ድንጋዮች በአሮጌ ሕይወታቸውና በአሮጌ ባሕሪያቸው የእስራኤልን አሥራ-ሁለት ነገዶች ያመለክታሉ—ኢያ. 4፡9፦

1. ጌታ እስራኤል በአሮጌ ባሕሪያቸው ከዮርዳኖስ የሞት ውኃ በታች እንዲቆዩ መፈለጉን በማመልከት ኢያሱ እነዚህን አሥራ-ሁለት ድንጋዮች በዮርዳኖስ መካከል ታቦቱ በነበረበት ስፍራ ተከላቸው።
2. ይህ የአማኞች አሮጌው ሰው በክርስቶስ ሞት ውስጥ መቆየት እንዳለበት በምሳሌ ያሳያል—ሮሜ 6፡6፤ ገላ. 2፡20፤ ፊልጵ. 3፡10።

መ. የአሥራ ሁለቱ ድንጋዮች ሁለት መደቦች አሮጌ ሰዎችን እንደተቀበረ እና ከሞት-የተነሣው አዲስ ሰዎችን ከሦስታንዱ አምላክ ጋር እንደ አንድ እየኖረና እየሠራ መሆኑን ያመለክታል፤ ይህ በኤፌሶን 2፡1፣ 4-6፣ 15፣ እና 10 ካለው መገለጥ ጋር አብሮ ይሄዳል።

## III. ካህናቱ ሕዝቡ ሁሉ ፈጽመው ዮርዳኖስን እስኪሻገሩ ድረስ የምስክሩን ታቦት ተሸክመው በዮርዳኖስ ወንዝ ታችኛው ክፍል በደረቅ መሬት ላይ ጸንተው ቆሙ—ኢያ. 3፡8፣ 13-15፣ 17፤ 4፡10-11፣ 15-18፦

ሀ. ታቦቱን የተሸከሙት ካህናት ወደ ውኃው ውስጥ ለመግባት ቀዳሚዎቹ ከውኃው ውስጥ ለመውጣት ደግሞ የመጨረሻዎቹ ነበሩ፤ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ እንዲሻገሩ በወንዙ ታችኛው ክፍል ሆነው ጠበቁ—3፡17፤ 4፡15-16።

ለ. እግዚአብሔር እስራኤላውያን ወደ ሕይወት ምድር መንገድ ይኖራቸው ዘንድ ካህናቱን በሞት ሥፍራ አስቀመጣቸው—ቁ. 10፦

1. የወንዙ ታችኛው ክፍል የሞት ሥፍራ ነው፤ ምቹ ወይም የሚስብ አይደለም።
2. በወንዙ የታችኛው ክፍል የምስክሩን ታቦት መሸከም ታላቅ መከራ ነው።
3. ጌታ በኢያሱ 3 እና 4 እንዳሉት ካህናት፣ ወደ ውኃው ውስጥ የሚገቡ፣ ማለትም፣ በቅድሚያ ወደ ሞት ውስጥ የሚሄዱ የሰዎችን ቡድን እየፈለገ ነው—3፡8፣ 17፦
   - ሀ. ቤተ ክርስቲያን የሕይወትን መንገድ እንድታገኝ በቅድሚያ በመስቀሉ ለመታደብ፣ በሞት ሥፍራ ለመቆም ፈቃደኞች ናቸው—2 ቆሮ. 4፡10-12።
   - ለ. ሌሎች ሕይወትን መቀበል ከመቻላቸው በፊት እግዚአብሔር እኛን በሞት ሥፍራ ማስቀመጥ አለበት—ዮሐ. 2፡19፤ 12፡24፤ 1 ቆሮ. 15፡36።

ሐ. ሐዋርያው ጳውሎስ በመሞት ሕይወትን ስላገለገለ፣ "ስለዚህ ሞቱ በእኛ ሕይወቱም በእናንተ ይሠራል" በማለት መመስከር ችሏል—2 ቆሮ. 4፡12፦

1. የሐዋርያት ሥራ ሕይወት በአማኞች ውስጥ ይሠራ ዘንድ የሞት ሥራ በእነርሱ ውስጥ መሥራቱ ነው—ቁ. 10-12።
2. ሞት እኛ ውስጥ የመሥራቱ ውጤት ድንቅ ነው—እርሱም በሌሎች ውስጥ ሕይወት ነው—ቁ. 12።
3. የአዲሱ ኪዳን አገልግሎት እውነተኛው ሥራ የመሥራት ጉዳይ አይደለም፤ የመሞት ጉዳይ ነው—ቁ. 1፤ 3፡8-9፤ 5፡18።
4. በጌታ ምለሳ ውስጥ ሕይወት በሌሎች ውስጥ ይሠራ ዘንድ መሞት ያስፈልገናል፤ ስለሆነም፣ መሞታችን መሥራታችን ነው—4፡12።
5. "ጌታ ሥራን እንድታከናውኑለት አይፈልግም። እንድትሞቱ ይፈልጋል። ከሞታችሁ ሕይወት በሌሎች ውስጥ ይሠራል። በመሞት ለሌሎች ሕይወትን ታገለግላላችሁ። ስለዚህ፣ ሥራችን መሞት ነው"—*Life-study of 2 Corinthians*, ከሚለው መጽሐፍ፣ ከገጽ 295 የተወሰደ።

## IV. ምንም እንኳን እስራኤልውያን ተቀጥተው፣ ሰልጥነው እና ብቁ ተደርገው የነበረ ቢሆንም፣ ዮርዳኖስን ከተሻገሩ በኋላ ያኔም ቢሆን ማጥቃት ከመጀመራቸው በፊት ተጨማሪ ዝግጅት ያስፈልጋቸው ነበር—ኢያ. 5፡1-10፦

ሀ. የዮርዳኖስን ወንዝ መሻገር በከነዓን ከሚገኙ ሰባት ነገዶች ጋር ለመዋጋት ነበር—4፡12-13።

ለ. ኢያሱ ዮርዳኖስን በመሻገር ውስጥ በነበረው ተዓምር ሲሳተፍ ሳለ፣ ከአጋንንታዊ ከነዓናውያን ጋር ለመዋጋት ቅድሚያውን ለመውሰድ በረታ—3፡6-7፣ 10፤ 4፡14።

ሐ. ያሕዌ “የእስራኤልን ልጆች ሁለተኛ ጊዜ [እንዲገርዛቸው]” ኢያሱን አዘዘው—5፡2፦

1. የመገረዝ አላማ በእግዚአብሔር ቃል የተገባውን ምድር እንዲወርሱ በእግዚአብሔር የተመረጡትን ሕዝብ አዲስ ሕዝብ ለማድረግ ነበር—ተዛ. ዘፍ. 17፡7-12።
2. አዲሱን እስራኤል መግረዝ አማኞች በእግዚአብሔር እንደተሰጣቸው እድል ፈንታ ክርስቶስን በትንሣኤ ይወርሱት ዘንድ የሥጋን ሰውነት በማስወገድ በአማኞች ላይ የሚተገበረውን በሞቱ የሆነውን የክርስቶስን መገረዝ በምሳሌ ያሳያል—ቆላ. 2፡11-12፤ 1፡12።
3. መንፈሳዊ መገረዝ በክርስቶስ ሞት ውስጥ የመቀበር መቀጠል ነው—ሮሜ 6፡3-4፦
   ሀ. የዮርዳኖስን ወንዝ በመሻገር፣ አሮጌው እስራኤል ተቀበረ፣ አዲሱ እስራኤል መጣ፤ ይህ በእግዚአብሔር የተደረገ ውጫዊ ሥራ ነበር።
   ለ. የእስራኤል ልጆች መገረዛቸው የዮርዳኖስን ወንዝ በመሻገር ውስጥ እግዚአብሔር ያደረገውን ነገር በተግባራዊ መንገድ መተግበራቸው ነበር—ኢያ. 5፡2-9።
4. በአዲስ ኪዳን መንፈሳዊ መገረዝ የክርስቶስ ሞት በሥጋችን ላይ ያለማቋረጥ መተግበር ነው—ፊልጵ. 3፡3፤ ቆላ. 2፡11፦
   ሀ. ምንም እንኳን በእውነቱ ወደ ክርስቶስ ሞት ውስጥ የተጠመቅን እና ከእርሱ ጋር የተቀበርን እና የተነሣን ቢሆንም፣ በተግባራዊነት ዕለት በዕለት የመስቀሉን መግረዝ በሥጋችን ላይ በመንፈስ መተግበር አለብን—ሮሜ 8፡13፤ ገላ. 5፡24።
   ለ. ይህ በክርስቶስ ሞት እና መቀበር ውስጥ የመቆየት እውነታ እና ተግባራዊነት ነው።

መ. የእስራኤል ልጆች በጌላገላ ሰፈሩ፣ በኢያሪኮም ሜዳ ፋሲካ አደረጉ—ኢያ. 5፡10፦

1. የፋሲካ በዓል የተደረገው በበኩር ወንድ ልጆቻቸው ላይ ከመጣው የሞት-ፍርድ ያሕዌ እስራኤልን መቤዠቱን እና ከግብጽ እና ከፈርኦን የጭቆና አገዛዝ ያሕዌ እስራኤልን ማዳኑን ለማሰብ ነበር—ዘጸ. 12፡3-7፣ 11-14፤ 14፡13-30።
2. ፋሲካን መጠበቅ ያሕዌ እስራኤልን ከፈርኦን እና ከግብጽ እንዳዳነ እንዲሁ፣ የከነዓንን ነገዶች እንደሚያጠፋ እና እስራኤልን ከእነርሱ ነጻ እንደሚያወጣ አመልክቷል—ኢያ. 5፡10።
3. እስራኤል ፋሲካውን መጠበቁ አማኞች ጌታን እንደ ቤዛቸው እና አዳኛቸው ለማሰብ የጌታን ማዕድ መጠበቃቸውን በምሳሌ ያሳያል—ማቴ. 26፡26-28።

*© 2021 Living Stream Ministry*